# ስለ ኮሎኖስኮፒ ምርመራ ገለጻ

*በሂሌል ያፌ የሕክምና ማዕከል*
*የጋስትሮኢንተሮሎግ ክፍል*

המרכז הרפואי
הלל יפה
מומחים באנשים

# የኮሎኖስኮፒ ምርመራ ምንድን ነው?




- ይህ ለታችኛው የመፍጫ ሥርዐት ክፍል በተጣጣፊ ቱቦ (ኢንዶስኮፒ) አማካይነት የሚደረግ ምርመራ ነው።
- የኢንዶስኮፒ መሣሪያ በሽታዎችን ለመመርመርና ለማከም ሲያስፈልግ ወደ ውስጥ ለማየት ያስችላል።
- ምርመራው ወደ ሰውነት ውስጥ አዝልቆ የማስገባት ሥራን ያካተተ በመሆኑ ሁኔታውን ዐውቆ መስማማትን በፊርማ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

המרכז הרפואי
הלל יפה
מומחים באנשים

# ምርመራው የሚካሄደው እንዴት ነው?





- ከምርመራው በፊት አረጋጊ አጭር ሽልብታ ፈጣሪ (አሸላቢ) ኬሚካል በመርፌ ይሰጣል።
- ምርመራው የሚካሄደው በግራ ጎን በኩል በመጋደም ነው።
- ኢንዶስኮፒው በፊንጢጣ በኩል ይገባል።

המרכז הרפואי הלל יפה מומחים באנשים

# የምርመራው ሂደት።




- ምርመራው በአማካይ የሚወስደው ጊዜ ከ 15 እስከ 30 ደቂቃ ያህል ሲሆን ከዚያም በላይ ሊራዘም ግን ይችላል።
- በምርመራው ሂደትም የትንፋሽና የልብ ትርታ ሁኔታ ክትትል ይደረጋል።
- አንዳስፈላጊነቱ በኢንዶስኮፒው በኩል ለምርመራ ወይም ለሕክምና የሚሆኑ ዕቃዎች (ቅንጣቢ ሥጋ ለመውሰድ እንደ መርፌ የመሰሉ ዕቃዎች) ይገባሉ።
- ከምርመራው ከተገገመ በኋላ - የውጤቶቹን ዝርዝር የያዘ መረጃ ይሰጣል።

המרכז הרפואי
הלל יפה
מומחים באנשים

# በኢንዶስኮፕ ሊከናወኑ የሚችሉ ሕክምናዎች




- ለምርመራ የሚሆን ቅንጣቢ (ባዮፕሲ) መውሰድ
- ፖሊፖችን መቁረጥ
- የሚደማ ቦታን መጥበስ
- ባዕድ ነገሮችን ማውጣት
- ጥበትን ማስፋት
- መመገቢያ ቱቦ ማስገባት
- አርቲፊሻል ቱቦ ማስገባት
- እና የመሳሰሉት

המרכז הרפואי
הלל יפה
מומחים באנשים

# ከምርመራው ጋር ግንኙነት ያላቸው እክሎች



የኮሎኖስኮፒ እክሎች ከስንት አንድ ይሁኑ እንጂ፣ ወደ ውስጥ ተዘልቆ ከሚሠሩ ሥራዎች የተነሣ ግን ሊከሰቱ ይችላሉ።

- ከምርመራ በኋላ የሚመጣ የሆድ ህመምና መቀብተት፤
- ድጋሚ ምርመራ ወይም የቀዶ ጥገና ጣልቃ ገብነት ሊያሻው የሚችል የመድማት ሁኔታ፤
- የቀዶ ጥገና ጣልቃ ገብነት የሚያሻው - የአንጀት ግድግዳ መሸርከት፤
- ለማደንዘዣው ኬሚካል አለርጂክ መሆን፤

המרכז הרפואי
הלל יפה
מומחים באנשים

# ለምርመራው መሰናዶ የሚደረገው እንዴት ነው?



- ✓ ለዚሁ ዐላማ የተዘጋጀውን ኬሚካል በመጠጣት ትልቁን አንጀት ከጋዝ ማጽዳት፤ በተቀበልከው ማብራሪያ ቅጽ ላይ እንደየመድኀኒቱ ዐይነት የአዘገጃጀትና የአመጋገብ መመሪያዎች ላይ የተዘረዘረውን በጥንቃቄ መከተል ያስፈልጋል።
- ✓ ከምርመራው በፊት ቢያንስ ለ 4 ሰዓታት ያህል በጾም መቆየት ያስፈልጋል።
- ✓ ከክፍሉ ከተለቀቅህ በኋላ አብሮህ ይሆን ዘንድ ከሰው ጋር መምጣት አለብህ።
- ✓ በማደንዘዣው ብዥታ ሳቢያ ከሕክምና በኋላ ለ 12 ሰዓታት ያህል መኪና ማሽከርከር የለም።

המרכז הרפואי
הלל יפה
מומחים באנשים

# ለምርመራው የሚደረግ ተጨማሪ መሰናዶ



- ✓ ከአካሚው ሐኪም ጋር የታካሚውን የቆዩ በሽታዎችና በዚህ ምረመራ ሊደረግ ያለውን የሕክምና ዐይነት ያገናዘበ ምክክር በማድረግ፣ የደም ማቅጠኛ መድኀኒቶችን፣ ምርመራው ከሚደረግበት ዕለት የተወሰኑ ቀናት በፊት ለማቆም ማሰብ ያስፈልጋል።
- ✓ የልብ ትርታ መቆጣጠሪያ መሣሪያ በውስጣቸው ላላቸው - ከጋስትሮው ክፍልና ከልብ ሐኪም ጋር አስቀድሞ በመመካከር መሰናዳት ያስፈልጋቸዋል።
- ✓ ታካሚው/ዋ ዕድሜው/ዋ ከ 18 ዓመት በታች የሆነና ዐውቆ/ቃ መስማማቱን/ቷን በፊርማው/ዋ ለማረጋገጥ የማይበቃ/ትበቃ ከሆነ/ች የወላጅ/ የወኪል ጣልቃ ገብነት ያስፈልጋል።

የጋስትሮኢንተሮሎጊያ ኮሚቴ ፍጹም ጤንነት ይመኝላችኋል፤ ይቅናችሁ።

המרכז הרפואי
הלל יפה
מומחים באנשים